JASIRI

Catalysing High-Impact Entrepreneurship in Africa

**ጋዜጣዊ መግለጫ | ጥር 6, 2016 ዓ.ም**

**ማስታወቂያ**

<u>የ ጃሲሪ ክህሎትን ሥራ ላይ የማዋል ፕሮግራም 6ኛ ዙር ማመልከቻ</u>

የ ጃሲሪ ክህሎትን ሥራ ላይ ማዋል ፕሮግራም 6ኛ ዙር ማመልከቻ አሁን ተከፍቷል። ጃሲሪ ከኬንያ፣ ከሩዋንዳ እና ከኢትዮጵያ የመጡ ሥራ ፈጣሪዎች እንዲያመለክቱ ጥሪ ያቀርባል። ፕሮግራሙ ጠንካራ ብቃትን መሰረት ያደረገ የአመራረጥ ሂደት በመከተል፤ በጣም ተስፋ ሰጭ እና ብቁ ስራ ፈጣሪዎችን ለፕሮግራሙ ይመለምላል።

አሁን ባለው ተለዋዋጭ የንግድ ዓለም ውስጥ አዲስ ሥራ መጀመር በጣም ከባድ ሊሆን ይችላል። ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎች የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች በመገንዘብ፣ ጃሲሪ ታለንት ኢንቬስተር በአለን እና ጊል ግሬይ ፊላንትሮፒስ ስር የሚንቀሳቀስ ልዩ ፕሮግራም ሲሆን፤ ከፍተኛ ተፅእኖ ያላቸውን፣ ግብይትን መፍጠር እና የጋራ እሴትን መሰረት ያደረጉ ሥራዎችን ለማዳበር ሥራ ፈጣሪዎችን ለመደገፍ ጽኑ እና ቁርጠኛ አቋም ያለው ነው። ጃሲሪ ታለንት ኢንቬስተር ለአዳዲስ ንግዶች ስኬት ማነቆ የሆኑ እንቅፋቶችን ለማስወገድ ይጥራል። ፕሮግራሙ ፈንድ በመስጠት፣ በማሰልጠን፣ በስትራቴጂካዊ ምክር እና በፈጠራ ውስብስብ ቦታ ላይ ድጋፍ በመስጠት፤ የፕሮግራሙን ተሳታፊዎች ከንግድ ሃሳብ እስከ ቬንቸር ፈጠራ እገዛ ያደርጋል።

“ጃሲሪ በሦስት የሥራ ፈጠራ አስፈላጊ ቅድመ-ሁኔታዎች ላይ መሰረት ያደረገ ሲሆን፤ እነርሱም፡- አልኬሚ፣ ምኞት እና አመለካከት ናቸው። ከአልኬሚ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሥራችን፤ ሥራ ፈጣሪዎችን ከዜሮ ወይም ከምንም እገዛ በማድረግ መምራት መቻላችን ነው። እንዲሁም ለወደፊት የአፍሪካ ብልጽግናን ለመቅረጽ የግብይት ፈጠራ እናስተዋውቃለን። ታቅዶበት የተሰየመው የፕሮግራማችን ስም ጃሲሪ፤ የስዋሂሊ ትርጓሜውም የጀግንነት ቃል ሲሆን ይህም ያለንን ቁርጠኛ አቋም እና መሰጠታችንን ያሳያል። ትልቅ ማሰብ፣ የወደፊቱን ግምት ውስጥ በማስገባት ለረጅም ጊዜ ማሰብ እና ኃላፊነት የተሞላበት ስነምግባር ያለው ስራ ፈጠራ ድፍረትን ይጠይቃል።” (አንቶኒ ፋር፤ የአላን እና ጊል ግሬይ ፊላንትሮፒስ ዋና ሥራ አስፈፃሚ)

ጉልህ የሆነ ተጽእኖ ማድረጋችንን የምንቀጥል ሲሆን፤ ከፕሮግራሙ ጅማሮ እስከ አሁን ድረስ 144 የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎችን በ4 ዙር ውስጥ በማፍራት ከ 61 ቬንቸር 24 ኢንዱስትሪዎችን አሳድገናል፤ በተጨማሪም ድርጅቶቻችን በአጠቃላይ ለ613 ሰዎች የስራ እድል ፈጥረዋል።

የስድስተኛው ዙር ማመልከቻ በጥር 15, 2016 ዓ.ም ተከፍቶ መጋቢት 27, 2016 ዓ.ም የሚያበቃ ይሆናል። ጃሲሪ ፍላጎት ያላቸው አመልካቾች የማመልከቻውን ሂደት በተመለከተ ሊያነሱ የሚችሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚረዳቸውን መረጃ በተለያዩ ጊዜያት በ ኦንላይን የሚያደርግ ሲሆን፤ ዝርዝር መረጃውም በጃሲሪ ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ ይገኛል።

ለማመልከት https://jasiri.org/application/ ይጎብኙ።

**ስለ ጃሲሪ**

ጃሲሪ በአፍሪካ አህጉር ላይ አዳዲስ ገበያዎችን በመፍጠር፤ ማህበረሰቡን የሚጠቅሙ እና ድህነትን ታሪክ የሚያደርጉ ስራ ፈጣሪዎች ላይ ኢንቨስት ያደርጋል፣ ያሳድጋል፤ እንዲሁም ያበረታታል። ጃሲሪ ሥራ ፈጣሪዎች ለአዳዲስ የፈጠራ ሥራዎች ቁልፍ ናቸው ብሎ በማመን፤ ሥራ ፈጣሪዎችን ተባበሪ መስራቾች ሊሆኑ ከሚችሉ ከፍተኛ ራዕይ የሰነቁ ሌሎች ሥራ ፈጣሪዎች ጋር እንዲገናኙ ዕድል ያመቻቻል። ፕሮግራሙ ከሀሳብ ማመንጨት እስከ ፈጠራ ድረስ አዳዲስ ስራዎችን በመደገፍ፤ በአፍሪካ ልዩ እና ኃላፊነት የሚሰማቸው ስራ ፈጣሪዎችን ለማፍራት የረጅም ጊዜ አካሄድ ይከተላል።

ተጨማሪ መረጃ jasiri.org. ላይ ያግኙ

ፕሮግራሙ ሙሉ በሙሉ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ስለሆነ የቋንቋው ክህሎት ሊኖሮት ይገባል።

**የሚዲያ ጥያቄዎች**

ስለ ጃሲሪ ለጥያቄዎች እና ለበለጠ መረጃ enquiries@jasiri.org ይጠቀሙ።